# ትንቢተ ፡ ዮናስ ።

(ክለሳ.1.20020507)

## ትንቢተ ፡ ዮናስ ፥ ምዕራፍ ፡ 1 ።

ምዕራፍ ፡ 1 ።

1 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ወደዐማቴ ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ ዮናስ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

2 ፤ ተነሥተኽ ፡ ወደዚያች ፡ ወደ ፡ ታላቂቱ ፡ ከተማ ፡ ወደ ፡ ነነዌ ፡ ኺድ ፥ ክፋታቸውም ፡ ወደ ፡ ፊቴ ፡
ወጥቷልና ፥ በርሷ ፡ ላይ ፡ ስበክ ።

3 ፤ ዮናስ ፡ ግን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ወደ ፡ ተርሴስ ፡ ይኰበልል ፡ ዘንድ ፡ ተነሣ ፤ ወደ ፡ ኢዮጴም ፡ ወረደ ፥ ወደ ፡
ተርሴስም ፡ የምታልፍ ፡ መርከብ ፡ አገኘ ፤ ከእግዚአብሔርም ፡ ፊት ፡ ኰብሎ ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ተርሴስ ፡ ይኼድ ፡
ዘንድ ፡ ዋጋ ፡ ሰጥቶ ፡ ወደ ፡ ርሷ ፡ ገባ ።

4 ፤ እግዚአብሔርም ፡ በባሕሩ ፡ ላይ ፡ ታላቅ ፡ ነፋስን ፡ አመጣ ፥ በባሕርም ፡ ላይ ፡ ታላቅ ፡ ማዕበል ፡ ኾነ ፥ መርከቢቱም ፡
ልትሰበር ፡ ቀረበች ።

5 ፤ መርከበኛዎቹም ፡ ፈሩ ፥ እያንዳንዱም ፡ ወደ ፡ አምላኩ ፡ ጮኸ ፤ መርከቢቱም ፡ እንድትቀልላቸው ፡ በውስጧ ፡
የነበረውን ፡ ዕቃ ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ ጣሉት ፤ ዮናስ ፡ ግን ፡ ወደ ፡ መርከቡ ፡ ውስጠኛው ፡ ክፍል ፡ ወርዶ ፡ ነበር ፥ በከባድ ፡
እንቅልፍም ፡ ተኝቶ ፡ ነበር ።

6 ፤ የመርከቡም ፡ አለቃ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ቀርቦ ፦ ምነው ፡ ተኝተኻል ፧ እንዳንጠፋ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያስበን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡
ተነሥተኽ ፡ አምላክኽን ፡ ጥራ ፡ አለው ።

7 ፤ ርስ ፡ በርሳቸውም ፦ ይህ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ በማን ፡ ምክንያት ፡ እንዳገኘን ፡ እናውቅ ፡ ዘንድ ፡ ኑ ፥ ዕጣ ፡ እንጣጣል ፡
ተባባሉ ። ዕጣም ፡ ተጣጣሉ ፥ ዕጣውም ፡ በዮናስ ፡ ላይ ፡ ወደቀ ።

8 ፤ የዚያን ፡ ጊዜም ፦ ይህ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ በማን ፡ ምክንያት ፡ እንዳገኘን ፡ እባክኽ ፡ ንገረን ፤ ሥራኽ ፡ ምንድር ፡
ነው ፧ ከወዴትስ ፡ መጣኽ ፧ አገርኽስ ፡ ወዴት ፡ ነው ፧ ወይስ ፡ ከማን ፡ ወገን ፡ ነኽ ፧ አሉት ።

9 ፤ ርሱም ፦ እኔ ፡ ዕብራዊ ፡ ነኝ ፤ ባሕሩንና ፡ የብሱን ፡ የፈጠረውን ፡ የሰማይን ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔርን ፡
አመልካለኹ ፡ አላቸው ።

10 ፤ እነዚያም ፡ ሰዎች ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ እንደ ፡ ኰበለለ ፡ ርሱ ፡ ስለ ፡ ነገራቸው ፡ ዐውቀዋልና ፥ እጅግ ፡
ፈርተው ፦ ይህ ፡ ያደረግኸው ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ አሉት ።

11 ፤ ባሕሩንም ፡ ሞገዱ ፡ አጥብቆ ፡ ያናውጠው ፡ ነበርና ፦ ባሕሩ ፡ ከእኛ ፡ ዘንድ ፡ ጸጥ ፡ እንዲል ፡ ምን ፡
እናድርግብኽ ፧ አሉት ።

12 ፤ ርሱም ፦ ይህ ፡ ታላቅ ፡ ማዕበል ፡ በእኔ ፡ ምክንያት ፡ እንዳገኛችኹ ፡ ዐውቃለኹና ፡ አንሥታችኹ ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡
ጣሉኝ ፥ ባሕሩም ፡ ጸጥ ፡ ይልላችኇል ፡ አላቸው ።

13 ፤ ሰዎቹ ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ምድሩ ፡ ሊመለሱ ፡ አጥብቀው ፡ ቀዘፉ ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ ባሕሩ ፡ እጅግ ፡ አብዝቶ ፡ ይናወጥባቸው ፡
ነበርና ፥ አልቻሉም ።

14 ፤ ስለዚህ ፥ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጮኸው ፦ አቤቱ ፥ እንደ ፡ ወደድኽ ፡
አድርገኻልና ፥ እንለምንኻለን ፤ አቤቱ ፥ ስለዚህ ፡ ሰው ፡ ነፍስ ፡ እንዳንጠፋ ፡ ንጹሕም ፡ ደም ፡ በእኛ ፡ ላይ ፡
እንዳታደርግ ፡ እንለምንኻለን ፡ አሉ ።

15 ፤ ዮናስንም ፡ ወስደው ፡ ወደ ፡ ባሕሩ ፡ ጣሉት ፤ ባሕሩም ፡ ከመናወጡ ፡ ጸጥ ፡ አለ ።

16 ፤ ሰዎችም ፡ እግዚአብሔርን ፡ እጅግ ፡ ፈሩ ፥ ለእግዚአብሔርም ፡ መሥዋዕትን ፡ አቀረቡ ፥ ስእለትንም ፡ ተሳሉ ።

http://www.gzamargna.net

www.ethiopianorthodox.org

## ትንቢተ ፡ ዮናስ ፥ ምዕራፍ ፡ 2 ።

ምዕራፍ ፡ 2 ።

1 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ዮናስን ፡ የሚውጥ ፡ ታላቅ ፡ ዓሣ ፡ አሰናዳ ፤ ዮናስም ፡ ሦስት ፡ ቀንና ፡ ሦስት ፡ ሌሊት ፡ በዓሣው ፡
ሆድ ፡ ውስጥ ፡ ነበረ ።

2 ፤ ዮናስም ፡ በዓሣው ፡ ሆድ ፡ ውስጥ ፡ ኾኖ ፡ ወደ ፡ አምላኩ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጸለየ ፥ እንዲህም ፡ አለ ፦

3 ፤ በመከራዬ ፡ ሳለኹ ፡ ወደ ፡ አምላኬ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጮኽኹ ፥ ርሱም ፡ ሰማኝ ፤ በሲኦልም ፡ ሆድ ፡ ውስጥ ፡
ኾኜ ፡ ጮኽኹ ፥ ቃሌንም ፡ አዳመጥኽ ።

4 ፤ ወደ ፡ ጥልቁ ፡ ወደ ፡ ባሕሩ ፡ ውስጥ ፡ ጣልኸኝ ፥ ፈሳሾችም ፡ በዙሪያዬ ፡ ነበሩ ፤ ማዕበልኽና ፡ ሞገድኽ ፡ ዅሉ ፡
በላዬ ፡ ዐለፉ ።

5 ፤ እኔም ፦ ከዐይንኽ ፡ ፊት ፡ ተጣልኹ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ወደ ፡ ቅዱስ ፡ መቅደስኽ ፡ ደግሞ ፡ እመለከታለኹ ፡ አልኹ ።

6 ፤ ውሃዎችም ፡ እስከ ፡ ነፍሴ ፡ ድረስ ፡ ከበቡኝ ፤ ጥልቁ ፡ ባሕር ፡ በዙሪያዬ ፡ ነበረ ፤ የባሕሩ ፡ ሣር ፡ በራሴ ፡ ተጠምጥሞ ፡
ነበር ።

7 ፤ ወደተራራዎች ፡ መሠረት ፡ ወረድኹ ፤ በምድርና ፡ በመወርወሪያዎቿ ፡ ለዘለዓለም ፡ ተዘጋኹ ፤ አንተ ፡ ግን ፥ አቤቱ ፡
አምላኬ ፥ ሕይወቴን ፡ ከጒድጓዱ ፡ አወጣኽ ።

8 ፤ ነፍሴ ፡ በዛለችብኝ ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ዐሰብኹት ፤ ጸሎቴም ፡ ወዳንተ ፡ ወደ ፡ ቅዱስ ፡ መቅደስኽ ፡ ገባች ።

9 ፤ ከንቱነትንና ፡ ሐሰትን ፡ የሚጠብቁ ፡ ምሕረታቸውን ፡ ትተዋል ።

10 ፤ እኔ ፡ ግን ፡ በምስጋና ፡ ቃል ፡ እሠዋልኻለኹ ፤ የተሳልኹትንም ፡ እከፍላለኹ ። ደኅንነት ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡
ነው ።

11 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ዓሣውን ፡ አዘዘው ፥ ርሱም ፡ ዮናስን ፡ በየብስ ፡ ላይ ፡ ተፋው ።

## ትንቢተ ፡ ዮናስ ፥ ምዕራፍ ፡ 3 ።

ምዕራፍ ፡ 3 ።

1 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ኹለተኛ ፡ ወደ ፡ ዮናስ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

2 ፤ ተነሥተኽ ፡ ወደዚያች ፡ ወደ ፡ ታላቂቱ ፡ ከተማ ፡ ወደ ፡ ነነዌ ፡ ኺድ ፥ የምነግርኽንም ፡ ስብከት ፡ ስበክላት ፡ አለው ።

3 ፤ ዮናስም ፡ ተነሥቶ ፡ እንደእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ ነነዌ ፡ ኼደ ፤ ነነዌም ፡ የሦስት ፡ ቀን ፡ መንገድ ፡ ያኽል ፡
እጅግ ፡ ታላቅ ፡ ከተማ ፡ ነበረች ።

4 ፤ ዮናስም ፡ የአንድ ፡ ቀን ፡ መንገድ ፡ ያኽል ፡ ወደ ፡ ከተማዪቱ ፡ ውስጥ ፡ ሊገባ ፡ ዠመረ ፤ ጮኾም ፦ በሦስት ፡ ቀን ፡
ውስጥ ፡ ነነዌ ፡ ትገለበጣለች ፡ አለ ።

5 ፤ የነነዌም ፡ ሰዎች ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመኑ ፤ ለጾም ፡ ዐዋጅ ፡ ነገሩ ፥ ከታላቁም ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ታናሹ ፡ ድረስ ፡
ማቅ ፡ ለበሱ ።

6 ፤ ወሬውም ፡ ወደነነዌ ፡ ንጉሥ ፡ ደረሰ ፤ ርሱም ፡ ከዙፋኑ ፡ ተነሥቶ ፡ መጐናጸፊያውን ፡ አወለቀ ፡ ማቅም ፡
ለበሰ ፥ በዐመድም ፡ ላይ ፡ ተቀመጠ ።

7 ፤ ዐዋጅም ፡ አስነገረ ፥ በነነዌም ፡ ውስጥ ፡ የንጉሡንና ፡ የመኳንንቱን ፡ ትእዛዝ ፡ አሳወጀ ፥ እንዲህም ፡ አለ ፦ ሰዎችና ፡
እንስሳዎች ፡ ላሞችና ፡ በጎች ፡ አንዳችን ፡ አይቅመሱ ፤ አይሰማሩም ፡ ውሃንም ፡ አይጠጡ ፤

8 ፤ ሰዎችና ፡ እንስሳዎችም ፡ በማቅ ፡ ይከደኑ ፥ ወደ ፡ እግዚአብሔርም ፡ በብርቱ ፡ ይጮኹ ፤ ሰዎችም ፡ ዅሉ ፡ ከክፉ ፡
መንገዳቸውና ፡ በእጃቸው ፡ ካለው ፡ ግፍ ፡ ይመለሱ ።

9 ፤ እኛ ፡ እንዳንጠፋ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተመልሶ ፡ ይጸጸት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ ከጽኑ ፡ ቍጣውም ፡ ይመለስ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡
ማን ፡ ያውቃል ፧



www.ethiopianorthodox.org

10 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ከክፉ ፡ መንገዳቸው ፡ እንደተመለሱ ፡ ሥራቸውን ፡ አየ ፤ እግዚአብሔርም ፡ ያደርግባቸው ፡
ዘንድ ፡ በተናገረው ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ተጸጸቶ ፡ አላደረገውም ።

ትንቢተ ፡ ዮናስ ፥ ምዕራፍ ፡ 4 ።

ምዕራፍ ፡ 4 ።

1 ፤ ይህም ፡ ዮናስን ፡ ክፉ ፡ ደስ ፡ አላሠኘውም ፥ ርሱም ፡ ተቈጣ ።

2 ፤ ወደ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ጸለየና ፦ አቤቱ ፥ እለምንኻለኹ ፤ በአገሬ ፡ ሳለኹ ፡ የተናገርኹት ፡ ይህ ፡
አልነበረምን ፧ አንተ ፡ ቸርና ፡ ይቅር ፡ ባይ ፥ ታጋሽም ፥ ምሕረትኽም ፡ የበዛ ፥ ከክፉው ፡ ነገርም ፡ የተነሣ ፡ የምትጸጸት ፡
አምላክ ፡ እንደ ፡ ኾንኽ ፡ ዐውቄ ፡ ነበርና ፥ ስለዚህ ፡ ወደ ፡ ተርሴስ ፡ ለመኰብለል ፡ ፈጥኜ ፡ ነበር ።

3 ፤ አኹንም ፥ አቤቱ ፥ ከሕይወት ፡ ሞት ፡ ይሻለኛልና ፥ እባክኽ ፥ ነፍሴን ፡ ከእኔ ፡ ውሰድ ፡ አለው ።

4 ፤ እግዚአብሔርም ፦ በእውኑ ፡ ትቈጣ ፡ ዘንድ ፡ ይገባኻልን ፧ አለ ።

5 ፤ ዮናስም ፡ ከከተማዪቱ ፡ ወጣ ፥ ከከተማዪቱም ፡ በስተምሥራቅ ፡ በኩል ፡ ተቀመጠ ፤ ከተማዪቱንም ፡ የሚያገኛትን ፡
እስኪያይ ፡ ድረስ ፡ በዚያ ፡ ለራሱ ፡ ዳስ ፡ ሠርቶ ፡ ከጥላው ፡ በታች ፡ ተቀመጠ ።

6 ፤ እግዚአብሔር ፡ አምላክም ፡ ቅል ፡ አዘጋጀ ፥ ከጭንቀቱም ፡ ታድነው ፡ ዘንድ ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ጥላ ፡ እንድትኾን ፡
በዮናስ ፡ ላይ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አደረጋት ፤ ዮናስም ፡ ስለ ፡ ቅሊቱ ፡ እጅግ ፡ ደስ ፡ አለው ።

7 ፤ በነጋው ፡ ግን ፡ ወገግ ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔር ፡ ትልን ፡ አዘጋጀ ፥ ርሷም ፡ ቅሊቱን ፡ እስክትደርቅ ፡ ድረስ ፡
መታቻት ።

8 ፤ ፀሓይም ፡ በወጣች ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔር ፡ ትኵስ ፡ የምሥራቅ ፡ ነፋስ ፡ አዘጋጀ ፡ ዮናስ ፡ እስኪዝል ፡ ድረስም ፡ ፀሓይ ፡
ራሱን ፡ መታው ፤ ለራሱም ፡ ሞትን ፡ ፈለገና ፦ ከሕይወት ፡ ሞት ፡ ይሻለኛል ፡ አለ ።

9 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ዮናስን ፦ በእውኑ ፡ ስለዚች ፡ ቅል ፡ ትቈጣ ፡ ዘንድ ፡ ይገባኻልን ፧ አለው ። ርሱም ፦ እስከ ፡
ሞት ፡ ድረስ ፡ እቈጣ ፡ ዘንድ ፡ ይገባኛል ፡ አለ ።

10 ፤ እግዚአብሔርም ፦ አንተ ፡ ትበቅል ፡ ዘንድ ፡ ላልደከምኽባት ፡ ላላሳደግኻትም ፥ ባንድ ፡ ሌሊት ፡ ለበቀለች ፥ ባንድ ፡
ሌሊትም ፡ ለደረቀችው ፡ ቅል ፡ አዝነኻል ።

11 ፤ እኔስ ፡ ቀኛቸውንና ፡ ግራቸውን ፡ የማይለዩ ፡ ከመቶ ፡ ኻያ ፡ ሺሕ ፡ የሚበልጡ ፡ ሰዎችና ፡ ብዙ ፡ እንስሳዎች ፡
ላሉባት ፡ ለታላቂቱ ፡ ከተማ ፡ ለነነዌ ፡ አላዝንምን ፧ አለው ፨



www.ethiopianorthodox.org